# የስብሰባ ጥሪ

# ለዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክስዮኖች በሙሉ

የዳሽን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 30ኛ (ሰላሳኛ) መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ስካይላይት ሆቴል ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

| | |
|---|---|
| የአክስዮን ማሕበሩ ስም | ዳሽን ባንክ አ.ማ. |
| የአክስዮን ማሕበሩ ዓይነት | የባንክ ስራ ውስጥ የተሰማራ የአክስዮን ማሕበር |
| የአክስዮን ማሕበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 10,748,686,000.00 |
| የአክስዮን ማሕበሩ የምዝገባ ቁጥር | 04/2/01821/88 |
| የአክስዮን ማሕበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ | አዲስ አበባ ፣ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09፣የቤት ቁጥር አዲስ |

## የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፡ -

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም
2. ምዕላተ ጉባዔውን ማረጋገጥ
3. የስብሰባ አጀንዳውን ማፅደቅ
4. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የነባር አክሲዮኖችን ግዥና ዝውውሮችን መወሰን
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
6. የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
7. የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን መወሰን
8. በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተወያይቶ መወሰን
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ሪፖርት ማዳመጥ እና ማፅደቅ
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ማከናወን
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ክፍያና አበል መወሠን
12. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

## ማሳሰቢያ

* በጉባኤው ላይ በግንባር መገኘት የማይችሉ ከሆነ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፊት ለፊት በሚገኘው የዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት 14ኛ ፎቅ የቦርድ ፅ/ቤት በመቅረብ የውክልና ቅፅ በመሙላት ከስብሰባው ከሶስት ቀን በፊት ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

* በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባኤው በአካል የምትገኙ ባለአክስዮኖች ማንነታችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ህጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትቀርቡ ተወካዮች የወካያችሁን ማንነት የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡

* በውል አዋዋይ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ ዋና ማስረጃውን እና ኮፒውን ይዞ በመቅረብ በስብሰባው ላይ መሳተፍ ይችላል፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ
ዳሽን ባንክ አ.ማ.